# ተቃዉሞየ ሌለቸውፍቺዎች በዲሲ

እርስዎና የትዳር አጋርዎ በፍቺ ሁሉም ጉዳዮ ተስማምተው ከሆነ እና አስፈላጊ የሆነ ውን ወረቀት ከፈረሙ ተቃዋሚየ ሌለው ፍቺ ያገኛሉ። “ሁሉም ነገር” ማለት ለመፋታት መስማማታችሁን እንዲሁም ስለ ልጆች ማሳደግ፣ የልጆች ማሳደግያ ድጋፍ፣ አበልና ንብረትና እዳ ክፍፍል ላይ መስማማት ነው። በሌላ አባባል፣ እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ በሁለታችሁ መካከል ፍርድ ቤቱ የሚፈታው ችግር እንደሌለ ተስማምታችኋል ማለት ነው።

## ተቃውሞየ ሌለውየ ፍቺ ሂደት እንዴት እጀምራለሁ?

ስለ ጉዳዮ ጠበቃን ማማከር ወይ እራስዎ ማስገባት ይችላሉ። አስፈላጊ የሆኑትን አቤቱታዎች (የፍርድ ቤት ወረቀቶች) በ www.dcbar.org/pleadings ወይም በ ዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማእከላዊ መቀበያ (500 Indiana Avenue NW፣ ክፍል JM-540) ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:30 a.m. እስከ 5:00 p.m በመሄድ ማግኘት ይችላሉ።

## ለፍቺውእምና መለከተው ማንኛችን መሆናችን ችግር አለው?

እርስዎ ወይ የትዳር አጋርዎ ለፍጹም ፍቺ ማመልከት ይችላሉ። ሌላኘው አካል የፍቃድ መልስ ይሞላሉ። ክሱን የሚያስገቡት ሰው ከሳሽ ሲሆኑ ሌላኛው ወገን ደግሞ ተከሳሽ ይሆናሉ። ፍቺው ተቃውሞ ከሌለው ከሳሽ ፍርድ ቤት ቀርበው በፍርድ ሂደት ላይ ቃላቸውን የሚሰጡ ሲሆን ተከሳሽ ፍርድ ቤት መምጣት ላይኖርባቸው ይችላል።

## ወረቀቱን የት አስገባለሁ?

ክስ ለማስገባት ወደ ዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማእከላዊ መቀበያ (500 Indiana Avenue NW) ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ፣ 8:30 a.m. እስከ 5:00 p.m በመሄድ ማስገባት ይችላሉ።

## ሌላ ምን ማስገባት አለብኝ?

እርስዎ የፈረመብት ክስና የትዳር አጋርዎ የተፈረመበት መልስ በተጨማሪ፣ ፍርድ ቤት የፍርድ ሂደት ቀጠሮ እንዲይዝሎት የሚጠይቀውን ተቃውሞየ ሌለውየ ጽሁፍ ትዛዝ ማስገባት ይኖርቦታል። እንዲሁም የቤተሰብ ፍርድ ቤት መስቀለኛ ማጣቀሻ መመላት ይኖርቦታል። እነዚህን የፍርድ ቤት ቅፆች ከማእከላዊ መቀበያ ማእከል ማግኘት ይችላሉ። ሲያስገቡ ከፃሀፊው ቀን ያለበት ማህተም የተመታ ቅጂ በመቀበል ለራስዎ መያዝ ይችላሉ። ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ተቃውሞየ ሌለውፍቺ ማስታወቅያ ይደርሶታል።

## ምን ያህል ገንዘብ ያስወጣል?

የማመልከቻ $80 መክፈል ይኖርቦታል (በጥሬ ወይ በገንዘብ ትእዛዝ)። መክፈል ካልቻሉ በዲሲ ክፍያ ያለመክፈል መረጃ ወረቀት ማንበብ ይኖርቦታል።

## ስምምነት ካለኝስ?

ስምምነት ፈርመውከነበረና የትዳር አጋርዎ ይህን እንደ ፍቺ ትእዛዝ ማካተት ከፈለጉ። ዳኛው ካካተቱ የትእዛዙ አካል በመሆን ወደፊት በቤተሰብ ፍርድ ቤት ውስጥ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ያለማክበር ሞሽን ላይ ተፈጻሚሊሆን ይችላል። ይህን ለማካተት ዳኛውን ካልጠየቁ፣ የትዛዙ አካል አይደለም እንዲሁም ወደፊት ሌላ ጉዳይ በመክፈት ብቻ ማስፈፀም ይችላሉ።

## ተከሳሹ ፍርድ ቤት መቅረብ አለባቸው?

የለባቸውም። ነገር ግን ከሳሽ የዲሲ ነዋሪ ካልሆኑና ተከሳሽ የዲሲ ነዋሪ ከሆኑ ወይም ተከሳሽ የቀድሞ ስማቸውን ማደስ የሚፈልጉ ከሆነ አንዳንድ ዳኞች ተከሳሽ ቢኖሩ ይመርጣሉ።

## ፍቺው የሚጠናቀቀው መቼ ነው?

ዳኛው ፍቺውን ከፈቀዱ ወዲያውኑ የፍቺውን ትዛዝ ወረቀት ቅጂ ያገኛሉ ወይም በፖስታ ቤት ይላክሎታል። ፍቺዎ የሚጠናቀቀው ፍቺ ወረቀቶን ካስገቡ በኋላ "ዶሴ ውስጥ የገባ" ብሎ ፍርድ ቤት ማህተም ከመታ ከ30 ቀናት በኋላ ሲሆን ይህም ከችሎትዎ በኋላ የተወሰኑ ቀናት ሊወስድ ይችላል።

ማንኛውም ወገን በ30 ቀናት ውስጥ ለፍርድ ቤት ይግባኝ በመጠየቅ የፍቺ ትእዛዙን እንዲቆይ (እንዲራዘም) መጠየቅ ይችላል። እንዲቆይ ከተፈቀደ፣ ይግባኝ ጥያቄው እስኪፈታ ድረስ ትእዛዙ አይጠናቀቅም። እንዲቆይ የተጠየቀው ጥያቄ ተቀባይነት ካላገኘ፣ የይግባኝ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ትእዛዙ ተፈፃሚ አይሆንም። ሁለታችሁም የዳኛው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ላለመጠየቅ ከተስማማቹ፣ በጋራ የይግባኝ መጠየቅ መብት ማንሳት ታስገቡና በመቀጠል 30 ቀናት መቆየት ሳያስፈልግ ውሳኔው ወዲያውኑ የመጨረሻ ይሆናል።

## የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡

በዲሲ ውስጥ የሚገኘውን በነጻ ገብተው መስተናገድ የሚችሉበትን የቤተሰብ ፍርድ ቤት የራስ አገዝ ማእከል ፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ 500 Indiana Avenue፣ NW፣ ክፍል JM-570 መጎብኘት ይችላሉ። ማእከሉ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:00 am እስከ 5:30 p.m. ክፍት ነው። ማእከሉ ሂደቱን ሊያስረዳዎት፣ አስፈላጊ የሆኑትን ህጋዊ ወረቀቶች ማጠናቀቅ እንዲችሉ ሊረዳዎ እንዲሁም ወደ ሌሎች ነፃ የሕግ ምንጮች ሊመሩዎት ይችላሉ። ነፃ የህግ ማማከር አገልግሎት አቅራቢዎችን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.lawhelp.org/dc ይጎብኙ ወይ ወደ ዲሲ ባር ሌጋል መረጃ የድጋፍ መስመር በ 202-626-3499 በመደወል ይህን ጉዳይ የሚመለከቱ መልእክቶችን ያዳምጡ።

## ተቃውሞ በሌለው ፍቺ ችሎት ውስጥ ዳኛው ምን ዓይነት ጥያቄ ሊጠይቁኝ ይችላሉ?

- እባክዎትን ስም፣ አድራሻና ስልኮን ለፍርድ ቤቱ ይግለፁ።
  - ለደህንነቶ የሚሰጉ ወይ ጥቃት እንዳይደርስቦት የሚሰጉ ከሆነ ለዳኛው ምትክ አድራሻ መስጠት እንደሚፈልጉ መናገር ወይ አድራሻዎን በሚስጢር ለዳኛው መስጠት እንደሚፈልጉ መናገር ይችላሉ።
- በኮሎምብያ ዲስትሪክት ውስጥ ለምን ያህል ግዜ ኖረዋል?
- በዚህ ጉዳይ ላይ ተከሳሹ ማን ነው?
  - ተከሳሹ የትዳር አጋርዎ ነው።
- እባክዎትን የትዳር አጋርዎን ስም፣ አድራሻና ስልክ ቁጥር ይናገሩ።
- የትዳ አጋርዎ ቢዚያ አድራሻ ላይ ለምን ያህል ግዜ ኖረዋል?
- መቼና የት ተጋባቹ?

- ዛሬ እዚህ የተገኙት ፍቺ ለመፈፀም ነው?
- የትዳር ምስክር ወረቀት አምጥተዋል? ይህ ቅጂ ነው?
    - የትዳር ምስክር ወረቀቶን ለዳኛው ፀሀፊ ይስጡ፤ እሳቸውም ለዳኛው ይሰጣሉ።
- የጋራ የወለዷቸው ወይ የሚያሳድጓቸው ልጆች አሉ? ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች ነው?
    - ምላሽዎ አዎ ከሆነ፣ ዳኛው የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሊጠይቁ ይችላሉ፡
    - እባክዎትን የልጆቹን ስም(ሞች)ና የተወለዱበትን ዘመን(ናት) ይናገሩ።
    - እያንዳንዱ ልጆች በአሁኑ ሰዓት የት ይኖራሉ?
    - ከዚህ በፊት ከማንኛውም ፍርድ ቤት የወጣ የማሳደግ፣ ጥየቃ ወይ ድጋፍ ትእዛዝ አለ?
    - እርስዎና የትዳር አጋርዎ ልጁን(ቹን) ስለ ማሳደግ ስምምነት አሎት?
    - እርስዎና የትዳር አጋርዎ ለማሳደግ ብቁ መሆኖን ያምናሉ (የጋራ የማሳደግ ፈቃድ ይኖሮታል)? እርስዎና የትዳር አጋርዎ ለማሳደግ የተሰጣቸው አሳዳጊዎች ብቁና ተገቢ መሆናቸውን ይስማማሉ (የጋራ የማሳደግ ፈቃድ ከሌሎት)?
    - ስምምነቶን መሰረት በማድረግ፣ ዳኛው፤ እርስዎና የትዳር አጋርዎ የመጠየቅያ መርሀግብር አዘጋጅተዋል? ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ።
    - የልጅ ማሳደግያ ድጋፍ ስምምነቶን መሰረት በማድረግ ዳኘው አሁንም፤ እርስዎና የትዳር አጋርዎ የልጆች ማሳደግያ ድጋፍ አመቻችተዋል? ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ። ስለ ዲሲ የልጆች ማሳደግያ ድጋፍ መመርያ ያውቃሉ? እርስዎና የትዳር አጋርዎ የሚሰሩበት መስርያ ቤት ስም፣ አድራሻና ስልክ ቁጥር? የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥርዎ? አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢዎ ስንት ነው? ለልጅዎ የጤና እንክብካቤና የራስዎ የጤና እንክብካቤ ወጪ ስንት ነው?
- እርስዎና የትዳር አጋርዎ ለተከታታይ ግዜ በጋራ ሳይኖሩ ያለ (ወሲባዊ ግንኙነት) ለምን ያህል ግዜ ተለያይተው ኖረዋል?
    - ከስድስት ወራ በላይ ነገር ግን ከአንድ ዓመት በታች ተለያይተው ከኖሩ፣ ዳኛው ሊጠይቁት የሚችሉት፤ እርስዎና የትዳር አጋርዎ የጋራ ስምምነት በፍቃደኝነት ለስድስት ወራት ተለያይተው ኖረዋል?
- ዛሬ እዚህ ውሳኔ ማግኘት ያለባቸው ማንኛውም የግል ወይ የንብረት መብት አለ (ቤት፣ መኪና፣ ጡረታ፣ የባንክ ሒሳብ ወይ ብድር የመሳሰሉ)?
- የከዚህ በፊት ስሞ እንዲመለስ (ሲወለዱ የነበሮት ስም) እየጠየቁ ነው?
    - መልስዎ አዎ ከሆነ፣ ዳኛው በተጨማሪ የሚጠይቁት፣ ጥያቄዎ የቀረበው ለሕገ ወጥ ወይ ማጭበርበር ዓላማ ነው?

## ያስታውሱ…

- በጋብቻ ስርአት አግብተው ከነበረ፣ የትዳር ምስክር ወረቀት ቅጂዎን ይዘው ይምጡ፥
- በማህበራዊ ሂደት አግብተው ከነበረ ማስረጃ ይዘው ይምጡ(ቃሎ እንደ ማስረጃ ነው)፡
- ጉዳዮን ዲሲ ውስጥ ለማስጀመር ፈልገው የዲሲ ነዋሪ ካልሆኑና የትዳር አጋርዎ የዲሲ ነዋሪነት ካላቸው፥ የሳቸውን ነዋሪነት የሚያሳይ ማስረጃ ወይ ራሳቸውን ይዘው ይምጡ፥
- ቀድመው ይገኙ (አንዳንድ ግዜ በፍርድ ቤት ጥበቃ ፍተሻ አልፎ ለመግባት ተጨማሪ ግዜ ይወስዳል) ነገር ግን ለመጠበቅ ዝግጁ ይሁኑ ምክንያቱም የእርስዎ ጉዳይ ከመጠራቱ በፊት ዳኛው ሌሎች ጉዳዮችን ሊያዩ ስለሚችሉ፡
- እዛው ሲደርሱ የፍርድ ቤቱን ፀሃፊ ይጠይቁ (ፀሀፊው በፍርድ ቤት ውስጥ ከዳኛው ፊት ለፊት ይቀመጣሉ)።